# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት እንደመሆኗ በፍትሕ መንፈሳዊ ድንጋጌ መሠረት በዓመት ሁለት ጊዜያት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤን ታደርጋለች፡፡

በዚሁ መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ በጥቅምቱ የ2002 ዓ.ም. ጉባኤ ዋዜማ ማለትም ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም. በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመገኘት

- እግዚአብሔር አምላክ ለሀገራችን፣ ለወገናችን ለዓለሙ ሁሉ ፍቅር አንድነቱን ሰላሙን እንዲሰጥልን፣
- ሕማመ ሥጋ አድሮባቸው በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዘው የሚሰቃዩትን እንዲያድንልን፣
- ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ የተለዩ ወገኖችን ሀገረ ሕይወትን፣ መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርስልን፣
- ዝናመ ምሕረቱን ዕክለ በረከቱን እንዲሰጠን ጸሎተ ምሕላን አድርሷል ፡፡

ቅዱስ ሲኖዶስ እንደተለመደው ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. መደበኛ ዓመታዊ ስብሰባውን በመቀጠል፣

1. በበጀት ዓመቱ የተከናወነውን የቅዱስ ሲኖዶስ የሥራ መግለጫ ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ በሪፖርቱ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ተቀብሎ አጽድቆታል ፡፡
2. ባለፈው ሐምሌ ወር 2001 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያናችን ተፈጥሮ ከነበረው የሥራ አለመግባባት ችግር የተነሣ ያልተጠበቀ አሳዛኝ ድርጊት ተፈጽሞ መገኘቱ ሁሉንም ያሳዘነ ቢሆንም፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ከሁሉ አስቀድሞ በአባላቱ መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ችግር መፍታት ተቀዳሚው አጀንዳ መሆን እንዳለበት በመገንዘብ ምልዓተ ጉባኤው በዕርቀ ሰላሙ ጉዳይ ላይ ከተወያየ በኋላ ችግሩ በዕርቅ እንዲፈታ ሆኖ ሰላም የሰፈነበትን ጉባኤ በማካሔድ መልካም ውጤት ተገኝቷል ፡፡
3. የአዲስ አበባን ሀገረ ስብከት በተመለከተም፣ ሀገረ ስብከቱ ካለው ስፋት አንፃር በዞን ደረጃ ተከፋፍሎ እንዲመደብ ማድረግ በማስፈለጉ የአመዳደቡ ሁኔታ አባቶች ካልተመደቡባቸው ከሌሎች አህጉረ ስብከት ጋር በአጥኚ ኮሚቴ ተመቻችቶ ለግንቦቱ የ2002 ዓ.ም. የርክበ ካህናት ጉባኤ ይቀርብ ዘንድ ምልዓተ ጉባኤው ተስማምቶ ወስኗል ፡፡

4. በተለያየ ምክንያት የሥራ ዝውውር እንዲደረግላቸው ጥያቄ ላቀረቡት ስድስት ሊቃነ ጳጳሳት የሥራ ዝውውሩ ተፈቅዷል ፡፡

5. በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሥር የሚተዳደሩ

ሀ/ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ፣
ለ/ የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያና
ሐ/ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የበላይ አመራር ሰጪነት እንዲተዳደሩ ተወስኗል ፡፡

6. በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ተዘጋጅቶ የቀረበው የ2002 ዓ.ም. በጀት ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ምልአተ ጉባኤው ተስማምቷል ፡፡

7. ከቤተ ክርስቲያኒቱ ኰሌጆች ተመርቀው ለሚወጡ ደቀ መዛሙርት ሊመደብ የሚገባ መነሻ በጀት፣ ጉዳዩ በሚመለከተው ኮሚቴ አማካኝነት ተጠንቶ ለግንቦቱ የ2002 ዓ.ም. የርክበ ካህናት ጉባኤ እንዲቀርብ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡

8. የብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምደባን በተመለከተ ከኮሚቴው አመዳደብ በፊት የመተዳደሪያ ደንቡ መቅደም ወሳኝነት ያለው አፈጻጸም ሆኖ ስለተገኘ ሕገ ቤተ ክርስቲያኑንና ቃለ ዓዋዲውን በማገናዘብ ሁለት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በአስረጅነት በሚገኙበት፣ ውስጠ ደንቡ በሕግ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ለግንቦቱ የ2002 ዓ.ም. የርክበ ካህናት ጉባኤ ይቀርብ ዘንድ ተወስኗል ፡፡

9. ምልዓተ ጉባኤው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት እንቅስቃሴዎቿን ለምትመራበት ለልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የተመደቡትን ኮሚሺነር ሹመት አጽድቆ ተቀብሎታል ፡፡

10. በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ረዳት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ሊመደቡበት የሚገባ ቦታ በአጥኚ ኮሚቴ ተመቻችቶ ይቀርብ ዘንድ ሦስት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሚገኙበት ኮሚቴ እንዲጠና በተደረገው መሠረት አጥኚ ኮሚቴው ጠቁሞ ካቀረባቸው አራት ድርጅቶች መካከል ብፁዕ አቡነ ሳመኤል ሊቀ ጳጳስ ከጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ግንቦቱ የ2002 ዓ.ም. የርክበ ካህናት ጉባኤ ድረስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ ሆነው እየሠሩ እንዲቆዩ ምልዓተ ጉባኤው ተስማምቶ ወስኗል፡፡

ከኢትዮጵያ ታሪክ እንደምንረዳዉ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህች ታሪካዊት ሀገር ለሰላም መስፈንና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ኀላፊነት አለባት፤ ይህም ሲባል የቤተ ክርስቲያኒቱንና የሀገሪቱን ታሪካዊ ትስስር መሠረት በማድረግ መሆኑን ባለመዘንጋት ነው ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ክርስቶስ ነው፤ ክርስቶስም የሰላምና የፍቅር ባለቤት ነው ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በኢትዮጵያ ሰላምና ፍቅር እንዲሰፍን ጥረት የምታደርገው፣ ስለፈለገች የምትሠራው፣ ስላልፈለገች ደግሞ የምትተወው ጉዳይ ሳይሆን ተግባርዋና ዓላማዋ ስለሆነ መንፈሳዊ ግዴታዋን ለመወጣት ነው ፡፡ በመሠረቱ ክርስቶስን መስበክ ማለት ፍቅርን፣ ማኅበራዊ ሰላምንና ስምምነትን

መስበክ ስለመሆኑ ብዙ ሐተታ አያስፈልግም፤ ምክንያቱም ራሱ ክርስቶስ ሰላማችን ነውና፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ጽኑዕ መሠረት ያላት የመሆኗን ያህል በዚህች ሀገር ሰላም እንዲሰፍን በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላት ሁላችንም እናውቃለን፤ ይልቁንም የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲፋጠኑ፣ የሰላሙ ሒደት እንዲሰፋ፣ እንዲስፋፋ መደማመጥ፣ መከባበር፣ መወያየትና አንዱ የሌላውን ሐሳብ መረዳት ያስፈልጋል፤ ይህ ዐይነቱ የተቀደሰ ልማድ ከሌለ ግን ማኅበራዊ ሕይወት ዋስትናን ያጣል ፡፡ ከዚህ አንፃር በየቤተ ክርስቲያኑ የሰላምና የዕርቅ እንዲሁም አብሮ በሰላም የመኖርና የመቻቻል ስሜት እንዲጎለብት ጥረት መደረግ አለበት ፡፡

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው በእግዚአብሔር ሰላም እንኖራለን እያልን በምንኖርበት አካባቢ ሰላም ከታጣ፣ መልካም ግንኙነትም ከጠፋ ከእግዚአብሔር ለመጣው ጥሪ፣ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለተሠዋለት ተልእኮ ቸልተኞች እንደሆን ይቈጠርብናል፡፡ ይህ እንዳይሆን የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ሁላችንም የሰላም ባህልን አዳብረን መኖር፣ በአኗኗራችንም የዓላማ መለያየት ለሚወገድበትና ሰላም ለሚሰፍንበት ሥነ ምግባር ተጠቃሽ ምሳሌዎች መሆን ይጠበቅብናል ፡፡

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ዛሬ ሁሉም እንደሚረዳው በሀገራችን ፍቅርና ሰላም ሰፍኖ ይታያል፤ ማናቸውም የእምነት ተቋም በነጻነት እንዲንቀሳቀስ መብቱ ተከብሮለታል ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ለኅብረተ ሰቡ ያላትን ታሪካዊ አለኝታ በቀጣይነት ይዛ መዝለቅ የምትችለው እስከ ዛሬ ድረስ ለኅብረተ ሰቡ ትሠራው የነበረውን እያጠናከረች፣ ወደፊትም የወቅቱን ሁኔታ ተከትላ መሥራት ስትችል ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሁሉም አቅጣጫ እስካሁን ያደረገቻቸው ጥረቶች የሚመሰገኑ ሆነው ይበልጥ ለመሥራት በሙሉ ኀይል እንድትነሣ ሕዝባችን ይጠብቃል፡፡

ቀደም ሲል በሐምሌ ወር 2001 ዓ.ም. ተፈጥሮ የነበረው ችግር በአባቶች ቀናናዊ ዕይታ የተፈታ ቢሆንም አፈጻጸሙ ቅዱስ ሲኖዶሱን በእጅጉ አሳዝኗል፤ ሆኖም ለሀገር አንድነትና ለወገን ደኅንነት ስትጸልይ የምትኖረው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የራሷን ችግር በራሷ የመፍታት አቅሟን አጎልብታ ባልተጠበቀ መንገድ ተከስቶ የነበረውን ችግር በመፍታት ዕርቀ ሰላሙን ለማስፈን በቅታለች ፡፡

ስለዚህ በሐምሌ ወር 2001 ዓ.ም. ተፈጥሮ የነበረውን ችግር ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደ ፈተና የምትቆጥረው ቢሆንም፣ አባቶች የሰጡትና የሚሰጡት ትምህርትና ቃለ ምዕዳን ትኩረትን አግኝቶ ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት በማስወገድ መፍትሔ መገኘቱን ሁሉም እንዲረዳው ያስፈልጋል ፡፡

እግዚአብሔር አምላካችን ለሀገራችንና ለዓለሙ ሁሉ ሰላሙን ይስጥልን ፡፡

**አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ (ዶ/ር)**
**ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**
**ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም**
**ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት**
**የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት**
**የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት**
ጥቅምት 15 ቀን 2002 ዓ.ም.